ቀን ጥቅምት 30 , 2006 ዓ.ም

**ለአሲምባ ድረገጽ አዘጋጆች**

**ከኃይለሚካኤል ጡሜቦ**

ጉዳዩ፡ **እርማት እንዲደረግ መጠየቅ**

ወድ የአሲምባ ድረገጽ አዘጋጆች በቅድሚያ የከበረ ሰላምታ አቀርባለሁ። ይህን አጭር ደብዳቤ ለመጻፍ ያስገደደኝ ምክንያት ከኢትዮምድያ ድረገጽ አግኝታችሁ በዳኛ ወልደሚካኤል መሸሻ “ **ጊዜ መስተወቱ !”  ተስፋዬ ገብረአብ ማነው** በሚል ርዕስ የቀረበውን መጣጥፍ በአሲምባ ድረገጽ ተጽፎ በመግኘቴ ነው። ጽሁፉ በማስረጃዎች የተደገፈ ለአንባቢ ብዙ እውነታዎችን የሚገልጽ ነው። በበኩሌ ትምህርት አግኝቻለሁ። ዳኛ ወልደሚካኤል መሸሻንም ለፈጸሙት ትልቅ ስራ አመሰግናቸዋለሁ።

ለዳኛ ወልደሚካኤል ፣ ለኢትዮሚድያ፣ ለአሲምባና ለአንባቢያን እንዲያውቁትና እንዲታረም የሚያስፈልግ ጉዳይ ስላላ ድረገጻችሁ መልእክቴን እንዲያተላልፍ በትሕትና እጠይቃለሁ። ለዳኛ ወልደሚካኤል በቀጥተ ልጽፍላቸው ፈልጌ ነበር በጽሑፋቸው ላይ ላገኛቸው የሚችልበት የኢሜል አድራሻ የለም ከኢትዮሚድያ ድረገጽ በስተቀር። ለኢትዮምድያም ስህተቱ እንዲታረም ደብዳቤ ጽፌለሁ ። ድረገጹም ስህተቱ እንደሚታረም መልስ ሰጥቶኛል። እስካሁን ግን እርማቱን በድረገጹ አልለጠፈም።በዳኛው ጽሑፍ ገጽ 43 **አጠቃለይ ጉዳዮች** በሚለው ስር አቶ ተስፋዬ ሀቢሶ በሽግግር መንግሥት ውስጥ የሀዲያን ሕዝብ እንደምወክል ሆኖ ቀርቧል። ትክክል አይደለም ። የሽግግሩን መንግሥት የመስረቱትና ቻርተሩን ያጻደቁት ሕዝብን ወከልን የሚሉ ድርጅቶች ናቸው። ለድርቶቹም በምን ያህል ሊወከሉ እንደሚችሉ የደለደለው ወያኔ ነው ።አቶ ተስፋዬ ሀቢሶ  የከምባታ ሕዝቦች ኮንግረስ (ክሕኮ) የሚል ድርጅት በማቋቋም ነው ወደ ሽግግሩ መንግሥት የገበውና የሽግግሩ መንግሥት ጻሐፊ በመሆን አገልግሎት የሰጠው። ከዚያም ወያኔ በደቡብ አፍሪቃ የኢትዮጵያ አምባሳደር አድርጎት ሾሚል። ተስፋዬ ሀቢሶ ብሔረሰቡ ከምባታ ነው። በሽግግር መንግሥትም ወክዬለሁ ያለው የከምባታን ሕዝብ ነው። የሀዲያ ብሔረሰብ ራሱን የቻለ ሕዝብ ነው። የሀዲያ ሕዝብ በሽግግር መንግሥት በአቶ ተስፋዬ ተወክሎ አያውቅም።በግለሰቡ ያልተወከለው ሕዝብ ቅሬታውን ማሳማቱ ደግሞ አግባብ ነው። እውነት መታወቅ አለበት። በመሆኑም ስህተቱ እንዲታረም በአክብሮት እጠይቃለሁ። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን የሀዲያንና የከምባታን ብሔረሰቦች አንድ አድርገው ያያሉ። ያ ስህተት ነው። ያም የሚሆነው በአገራችን ያሉትን ብሔረሰቦች በደንብ ከአለማወቅ የተነሳ ነው ብዬ እገምታለሁ። አገራችን- ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሔርሰቦች የሚገኙባት ነች። ሁሉንም ማወቅ ግዴታችን ሊሆን ይገባል። የሰውን አገር ታሪክ ጠንክረን እንደምንማር ሁሉ የአገራችን ታሪክ አካል የሆኑትን ብሄረሰቦች ለማወቅ ጥረት ብናደርግ ጥሩ ነው።

አመሰግናለሁ